# የኤርትራ መንግስት ሰሞነኛው አስቂኝ "ሩጫ"

**ዘሩባቤል ማቲያስ**

01/16/14

አይጋ ፎረም የተሰኘው ድረ-ገፅ ከመሰንበቻው የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአስመራው አስተዳደር ያለ አንዳች የፖሊሲና የባህሪ ለውጥ የተጣለበትን ማዕቀቦች ለማስነሳት በዲፕሎማቶቹ በኩል እየሮጠ መሆኑን ያወጣውን መግለጫ አስነብቦን ነበር። በመግለጫው ላይ በግልፅ እንደተመለከተው፣ የአቶ ኢሳያስ መንግስት ከሽብርተኞች ጋር ያሰረውን የጋብቻ ቀለበት ሳያወልቅ፣ ቀጣናውን የማተራመስ ፖሊሲውን ሳይተው እንዲሁም ለአል-ሸባብና ለሌሎች የሶማሊያ ታጣቂዎች የሚሰጠውን ሎጀስቲካዊም ይሁን ወታደራዊ ድጋፍ ሳያቋርጥ በመንግስታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ከአንዴም ሁለቴ የጣለበትን ማዕቀቦች ለማስነሳት በማድረግ ላይ የሚገኘው "ሩጫ" አስቂኝ ነው። ምክንያቱም የሻዕቢያው ቡድን ተግባርና ባህሪያዊ ማንነት ለየቅል ናቸውና—"ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ" እንዲል የሀገራችን ሰው።

እርግጥ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው፣ ባለፉት ጊዜያት የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር የሚታወቀው "ጠብ ያለሽ በዳቦ" እያለ ምስራቅ አፍሪካን ሀገራት በአጭር እና በረጅም ርቀት የሁከት "ሩጫ" በማካለሉ ሳቢያ የፀጥታው ምክር ቤት እንደ አንገት ሃብል የማዕቀብ ሜዲያሎችን ያጠለቀለት መሆኑን ነው። ግና ሰሞኑን በስመ-ዲፕሎማሲ ያለ ምንም ባህሪያዊ ለውጥ እነዚህን ማዕቀቦች ለማስነሳትና ከደረሰበት የመገለል ዕጣ- ፈንታ በቅጥፈት ለመፈወስ እያደረገ ያለው "ሩጫ" የት ሊያደርሰው እንደሚችል የሚያውቀው እርሱ ብቻ ነው። ለምን? ቢባል፣ ምንም እንኳን የኤርትራው መንግስት ሁሌም ቢሆን "ዓይኔን ግንባር ያድርገው" በሚል ያረጀ ያፈጀ ዲፕሎማሲ የሚመራ ቢሆንም፣ አሁን በሚገኝበት "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" ዓይነት ማንነቱ እየተመራ 'ማዕቀቦቹ ይነሱልኝ' እያለ ማቄን ጨርቄን ሳይል በየቦታው መሮጡ ሃቁን በሚያውቁት ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ይሁን የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ-መንግስታት

ባለስልጣን (ኢ.ጋድ) በኩል ቅቡል ሊሆን ስለማይችል ነው። እናም ሰሞነኛው የሻዕቢያ “ሩጫ” ታታሪዎቹ ጃፓኖች “የምትለውን እንዳልሰማህ ምግባርህ ይጮህብኛል” እንደሚሉት ዓይነት ከመሆን የሚዘል አይመስለኝም—ተግባርና ወሬ ለየቅል ናቸውና።

ያም ሆነ ይህ ግን እዚህ ላይ “የአስመራውን መንግስት እንዲህ አቅሉን አስተውት እያሮጡት ያሉት ማዕቀቦች እንደምን ያሉ ናቸው?፣ ‘ማዕቀቦቹ ይነሱልኝ’ እያለ በሌለ ማንነቱ የሚደሰኩረውስ ምን ዓይነት ፖሊሲ ነክና ባህሪያዊ ለውጦችን አምጥቻለሁ ብሎ ይሆን? እንዲሁም ከዲፕሎማቶቹ ሩጫ በስተጀርባ ያለው ትክክለኛ ፍላጎት ምንድነው?” የሚሉ ጥያቄዎችን ዘርዘር አድርገን በማንሳት ጉዳዩን መመልከት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ምክንያቱም እነዚህ አንኳር ነጥቦች የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ዛሬም ድረስ ነብር ዥንጉርጉርነቱን እንደማይቀይረው ሁሉ፤ እርሱም በቀጣናው ውስጥ የሚከተለውን የትርምስ ስትራቴጂ አለመቀየሩንና ከአሸባሪዎች ጋር የመሰረተውን “ጋብቻ” ፍቺ አለመፈፀሙን ብሎም ከከባቢው ሀገራትን አተራማሽነቱ አልፎ በዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ (DRC) እና በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ (CAR) ግጭቶች ውስጥ ሳይቀር እጁን የመዶሉን ሃቆች ውድ አንባቢዎቼ እንዲገነዘቡት ስለሚያደርግ ነው።

ታዲያ ወደ ዕውነታዎቹ ጓዳ መዝለቅ ይቻለን ዘንድ፤ በቅድሚያ አቶ ኢሳያስ የሚመሩትን መንግሰት ገና ከጅምሩ አንስቶ ምን እንደሚመስል ተፈጥሮአዊ ማንነቱን መመልከት ያስፈልጋል።...እናም ነገሩ እንዲህ ነው።...ከዛሬ አርባና ሃምሳ ዓመታት በፊት ሳህል በረሃ ላይ ራሱን “ህግሓኤ” (ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ) በሚል ስያሜ አቋቁሞ ለነፃነት ሲታገል የነበረውና ከኤርትራ ነፃነት በኋላም በመንግስትነት ተደራጅቶ ከማንነቱ ጋር የማይገናኘውን “ህግደፍ” (ህዝባዊ ግንባር ለፍትህና ለዴሞክራሲ) የሚል ስም ለራሱ የቸረው ሻዕቢያ፤ በፀረ-ዴሞክራሲያዊነት፣ ወታደራዊ ጀብደኝነትና በጥገኝነት የአስተሳሰብ ማዕበሎች የተዋጠ መሆኑን ማንነቱን አብጠርጥረው የሚያውቁ ወገኖች ይናገራሉ።

እርግጥም በአቶ ኢሳያስ ይመራ የነበረው ሻዕቢያ በመጀመሪያ ሳህል ተራራ ላይ ቁጭ ብሎ ነበር—ሁለት እግሮቹን አነባብሮ። በእነዚያ ጭው ባሉ የተራራ ሰንሰለቶች ላይም ፀረ-ዴሞክራሲያዊነትን፣ ወታደራዊ ጀብደኝነትንና ጥገኝነትን ልቅም አድርጎ ተማረ። ተምሮም አላበቃም—የድርጅቱ የህይወት ማጣፈጫ ቅመም አድርጎ በመጠቀም ከማርና ከወተት ይበልጥ እንዲጣፍጡት አደረጋቸው።...ይህን ማንነቱን ይዞም የደርግ ግብዓተ-መሬት ሲፈፀም አስመራ ውስጥ በመንግስትነት ከተመ። መቼም ፀረ-ዴሞክራሲያዊነትና

ጥገኝነት እንዲህ በቀላሉ የሚለቁ ዛሮች ባለመሆናቸው፤ ሁሉም ነገር እንደ ሳህል ተራራው እሳቤ የመሰለው የአስመራው አስተዳደር በህግና በስርዓት የሚመራ መንግስት መሆኑን ዘንግቶት ራሱን ከእነዚያ ተራሮች በላይ በመቆለል አካባቢውን ያምሰውና ያተራምሰው ገባ።

ከኤርትራ ነፃነት ማግሥት ጀምሮ ኢኮኖሚውን በሌሎች ሀገሮች አንጡራ ሀብት ላይ ተንጠልጥሎ በጥገኝነት ለመምራት ሲጥር የነበረው የአሥመራው ቡድን፤ የተጣባው የጥገኝነት ተውሳክ ህልም ሆኖ ከቅዥትነት ያላለፈ መሆኑን በመረዳቱ "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" በሚል እሳቤ የአፍሪካን ቀንድ የትርምስ አውድማ ለማድረግ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም፡፡ ማጥ ውስጥ የገባውን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከማሳደግ ይልቅ ሥራዬ ብሎ የትርምስ ስትራቴጂ በመንደፍ በአካባቢው ሀገራት ውስጥ ባሉት ግጭቶች ላይ ነዳጅ ያላርከፈከፈበት ወቅት የለም፡፡

ቀደም ሲል ከአሥመራ ጀምሮ በሀገራችን አልፎ እስከ ሞቃዲሾ ድረስ ዘርግቶት የነበረው የትርምስና የጥፋት መረብ በጀግናው መከላከያ ሠራዊታችንና በሀገራችን ህዝቦች ንቁ ተጋድሎና ተሳትፎ በመበጣጠሱ ሳቢያ፣ ፊቱን ወደ ሶማሊያ በማዞር በዓለም መንግሥታት ዕውቅና የተሰጠውን የሀገሪቱን ፌዴራላዊ የሽግግር መንግስት ለመጣል በይፋ አውጆ ተንቀሳቅሷል፡፡ ሠላማዊ ኑሮና የልማት እንቅስቃሴ ምንጊዜም የሚያስደነግጠው አምባገነኑ የኢሳያስ መንግሥት፤ "ጭር ሲል አልወድም" የሚለው ፖሊሲውን ገቢራዊ ለማድረግ ከፅንፈኛው እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረትና አል-ሸባብ እያለ ራሱን በሚጠራው የአሸባሪዎች ስብስብ አማካኝነት በሶማሊያ ልሳነ-ምድር ያላስተኮሰው ጥይትና ሮኬት፣ ያላስወረወረው ቦምብና ያላስቀበረው የፈንጂ ዓይነት የለም፡፡

በአንድ በኩል የተለያዩ የአለም አቀፍ ሚዲያ ጋዜጠኞችን በየጊዜውና በየተራ ወደ አሥመራና ምጽዋ እየጠራ "የሶማሊያውያንን ችግር መፍታት ያለበት በሶማሊያውያን ነው" እያለ የበግ ለምድ ለብሶ የሠላምን አስፈላጊነት በተራ ፕሮፖጋንዳ የሚደሰኩሩት የአስመራው ቡድን፤ በሌላ በኩል ደግሞ አል-ሸባብን ለመሳሰሉ አሸባሪና ጽንፈኛ ቡድኖች የሎጀስቲክስና የፋይናንስ ድጋፍ በመስጠትና በማስታጠቅ በሀገሪቱ እየጐለበተ ያለውን አንፃራዊ የሠላም ጭላንጭል ለማዳፈን ተሯሩጧል። ሻዕቢያ ኢኮኖሚውን እንደ ካሮት ቁልቁል እያሳደገና ህዝቡን ለአስከፊ ድህነትና እንግልት እየዳረገ በየጊዜው ሶማሊያ ውስጥ በተለያዩ የአውሮፕላን በረራዎችና በትላልቅ ጀልባዎች ለአሸባሪዎች በገፍ የሚያቀርባቸው

የነፍስ ወከፍ መሣሪያዎች፣ ሮኬቶች፣ ፈንጂዎችና ቦምቦች የመንግስቱን ፀረ-ጎረቤት ሀገር ራዕይና ፀረ-ህዝብ አመለካከት ቁልጭ አድርገው ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አሳይተዋል፡፡

ወታደራዊ ጀብደኝነት የተጠናወተው የኤርትራው መንግስት፣ በአፍሪካ ቀንድ የትርምስ ስትራቴጂው ውስጥ በአጀንዳነት ኢትዮጵያን፣ ሶማሊያን፣ ጅቡቲን፣ ሱዳንንና የመንን በመያዝ መበጥበጡና ማተረማመሱ የሚዘነጋ አይደለም። ይህ ቀጣናዊ አዋኪነቱ አልበቃው ብሎትም ባህር ተሻግሮ በመካከለኛው ምሥራቅና በሰሪላንካ ከባቢዎች የሽብር መረቡን በመዘርጋት ራሱን የቀጣናው አድራጊ ፈጣሪ አድርጎ በመሾም 'ዘራፍ እኔ የአሸባሪዎች አለቃ' እያለ ራሱ በፈጠረው ግጥምና ዜማ ዳንኪራ ተውረግርጓል፡፡ ዜማዊ ዳንኪራው ግን ስልተ-ምቱን የሳተ ስለነበር የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዓይን ሊያርፍበት ችሏል። እናም እነዚህን እኩይ የትርምስ ተግባሮቹን በራሱ የቅኝት መንገድ አጣሪ ቡድን መድቦ በጥብቅ ሲከታተለው የነበረው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤ በፀጥታ ምክር ቤቱ አማካኝነት የሻዕቢያውያን አስተዳደር "ለአካባቢው ሠላምና መረጋጋት አደገኛ ነው" በማለት የመሳሪያና የባለስልጣናት ዝውውር ዕገዳን ያካተተ የመጀመሪያውን ማዕቀብ ጥሎበታል፡፡

የሁለተኛው ማዕቀብ አነሳሽ ምክንያት ደግሞ እንዲህ ነበር።...የአቶ ኢሳያስ መንግስት በመጀመሪያው ማዕቀብ ምክንያት ራሱን ከግብረ-ሽበራ ተግባር ቆጥቦና ከቀጣናው ሀገራት ጋር ተስማምቶ መኖር ሲገባው፤ እርሱ ግን ብሶበት ተገኝቷል። በወቅቱ የመንግስታቱ ድርጅት የመደበው አጣሪ ቡድን ከድርጅቱ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ከባቢ ያለውን ሁኔታ በጥልቀት ሲያጠና ቆይቶ ባለ 417 ገጽ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ ሪፖርቱ ከዚህ በፊት ለመንግስታቱ ድርጅት ከቀረቡት መረጃዎች ተመሳሳይነት ባለው መልኩ የአቶ ኢሳያስ መንግስት የፀጥታው ምክር ቤትን የመሳሪያ ዕገዳ ማዕቀብን በመጣስ የሽብር ተግባሩን አጠናክሮ መቀጠሉን ይተነትናል፡፡ በገለልተኝነትና በጥንቃቄ የተጠናቀረው ይህ ሪፖርት፤ የአስመራው አስተዳደር እንደ ሃሺሽ በቦምብና በፈንጂ ጪስ "ሳይጀነጅን" የማያድርበት ቀን የሌለ መሆኑንም አጋልጧል፡፡ በሶማሊያ የተለያዩ ቦታዎች ውስጥ በአል-ሸባብ አማካኝነት የተፈፀመው የቦምብ ጥቃት፣ በአዲስ አበባው የአፍሪካ ህብረት 16ኛው ልዩ የመሪዎች ጉባዔ ላይ ሊቃጣ የነበረው የፈንጂ ናዳ እንዲሁም በተለያዩ የመዲናችን ከባቢዎች ሊከናወኑ የነበሩ የቦምብ

ፍንዳታዎች የተቀናበረው ጄኔራል ጠዓመ ጐይቶኦም የተባለ ግለሰብ በሚመሩት የሻዕቢያ የውጭ ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ቢሮ መሆኑንም የቡድኑ ሪፖርት ይፋ አድርጓል፡፡

ጉደኛው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር "ነጻ አውጪ" እያለ ከሚያንቆለጳጵሱት አሸባሪው አል-ሸባብ ጋር ያላቸው ቁርኝትም በሪፖርቱ ላይ ተተንትኗል፡፡ ሻዕቢያ ለሶማሊያው የሽብር ቡድን ወታደራዊ ስልጠና ኤርትራ ውስጥ ከመስጠትና መሳሪያ ከማስታጠቅ ባሻገር አንድ አስገራሚ ድርጊትም መፈፀሙ ተደርሶበታል፡፡ ይኸውም አል-ሸባብን ልክ እንደ ኤርትራ የመንግስት ሠራተኛ "ፔይሮል" ላይ ስሙን በማስፈር በየወሩ 80 ሺህ ዶላር ኬንያ በሚገኘው ኤምባሲው አማካኝነት ደመወዝ ሲሰጠው መቆየቱ ነው፡፡ ይህ ብቻም አይደለም– ቀደም ሲል የመንግስታቱ ድርጅት የኤርትራ መንግስት በኃይል ወርሮ ከያዛቸው የጂቡቲው ራስ ዱሜራ ኮረብታዎች በአስቸኳይ ለቅቆ እንዲወጣ መግለጫ ቢያወጣም 'አሻፈረኝ' ብሎ እዚያው መፅናቱን አጣሪ ቡድኑ ገልጿል። አል-ሸባብ ኡጋንዳ- ካምፓላ ውስጥ ከ76 በላይ ንፁሃን ዜጎችን የገደለበት ሲ-4 የተሰኘ ተቀጣጣይ ፈንጂ፤ አቶ ኢሳያስ በ16ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ በአሸባሪው "ኦነግ" ሰዎች አማኝነት ለማፈንዳት ታስበው ከነበሩትና ከተያዙት ፈንጂዎች ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ጭምር።

ይህ ብቻ አይደለም። የኤርትራ መንግስት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 1907 (2009)ን በመተላለፍ፤ የጂቡቲ፣ የኢትዮጵያ፣ የሱዳንና የኡጋንዳ ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎችን እና አሸባሪዎችን በማሰልጠን፣ የገንዘብና የሎጂስቲክስ ድጋፍ ማድረጉ ተረጋግጧል፡፡...እንግዲህ እነዚህን የአጣሪ ቡድኑን ዕውነታዎች የተገነዘበው እንዲሁም ከኢጋድና ከአፍሪካ ህብረት ተጨማሪ መረጃ ያገኘው የተመድ የፀጥታው ምክር ቤት በአስመራው መንግስት ላይ ቀደም ሲል ከተጣለበት ማዕቀብ በተጨማሪ የባለስልጣናትና የገንዘብ ዝውውር ዕገዳን ብሎም ሻዕቢያ ለመሳሪያ ግዥ የሚጠቀምበትንና ውጭ ካሉት ዜጎቹ የሚሰበስበውን የሁለት በመቶ ቀረጥ ሀገራት እንዲከለክሉ የሚያካትተውን ሁለተኛውን ማዕቀብ ጥሎበታል።...እርግጥ የኤርትራው አስተዳደር እነዚህን ማዕቀቦች አክብሮ ከነበረው የአሸባሪዎች ግብረ-አበርነት ሚና መላቀቅ ይገባው ነበር። ይሁን እንጂ የአቶ ኢሳያስ መንግስት "ከአሸባሪነት ስራዬ የሚለየኝ የለም" ብሎ የማለ ይመስል ዛሬም ከዚሁ ዓለም ካወቀው ተግባሩ አለመላቀቁን ሰሞኑን ገለልተኛው የተመድ አጣሪ ቡድን በሪፖርቱ ይፋ አድርጓል።

ታዲያ እዚህ ላይ 'የአስመራው አስተዳደር ምን ዓይነት ተጨባጭ ባህሪያዊ ለውጥ አምጥቶ ነው መፅቀቦቹ ይነሱልኝ በማለት ሰሞኑን አዲስ ሩጫ የጀመረው?' የሚል ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል።…እናም እስቲ ወደ ዕውነታው ጓዳ እንዲህ እንዝለቅ።…በቅርቡ የስራ ዘመኑ ከሁለቱ ማዕቀቦች በኋላ የተራዘመለት በመንግስታቱ ድርጅት የኤርትራና የሶማሊያ ጉዳይ አጣሪ ቡድን፤ የአቶ ኢሳያስ መንግስት ማንነትን "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም" እንዲሉት ዓይነት መሆኑን እንዲህ ሲል ገልፆት ነበር።…

*"…የኤርትራ መንግሥት ቀደም ሲል ሁለት ጊዜ በጦር መሣሪያና በሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር የተጣለበትን ማዕቀቦችን በመጣስ በሶማሊያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብነቱን ቀጥሏል። የአስመራው አስተዳደር አል-ሸባብን ጨምሮ ለተለያዩ የሶማሊያ የጦር አበጋዞች የመሣሪያ ዕርዳታ በማድረግ ሀገሪቱን የማተራመስ ስትራቴጂውን ዛሬም አልቀየረም።…"*

እርግጥም ይህ የአጣሪ ቡድኑ አባባል የኤርትራ መንግስት ከሁለቱ ማዕቀቦች በኋላም ቢሆን ከሽብርተኞች ጋር ያለውን ቁርኝት አለመተውን የሚያረጋግጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የአስመራው ቡድን የቀጣናውን ሀገራት አሸባሪዎችና ፀረ-ሰላም ሃይሎችን በጉያው ውስጥ አቅፎ በየሀገራቱ የልማትና የዴሞክራሲ ባህል ግንባታ ላይ እንቅፋት ለመፍጠር ያልሞከረበት ጊዜ እንደሌለ ተመስክሮበታል። ሌላውን ትተን በአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የሚመራው የኤርትራ መንግስት ሀገራችን ላይ በሽብር ሴራ የተተበተቡ የጥፋት እጆቹን የሰነዘረበትን የቅርቡን የአፋር ክልል ክስተትን መጥቀስ ይቻላል።

የአስመራው መንግስት "ሠላምና መረጋጋት ኢትዮጵያ ውስጥ የለም" የሚል ስዕል ለመፍጠር በየማሰልጠኛዎቹ በአምሳያው ጠፍጥፎ የሚሰራቸውን እንደ ኦነግ፣ ኦብነግ፣ ግንቦት 7 ወዘተ. የመሳሰሉ የሽብር ተላላኪዎቹን እያስታጠቀ ወደ ሀገራችን አሰርጎ በማስገባት ከልማት ጉዟችን ሊያሰደናቅፈን መጣሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከማዕቀቦቹ በኋላም ቢሆን  በዓለም አቀፉ ህግ የሚሳለቅና ከለመደው የግብረ - ሽበራ ተግባር ምንም ዓይነት ማዕቀብም ሆነ ማስጠንቀቂያ ሊያግደው እንደማይችል በድርጊቱ በይፋ ገልጿል–በአፋር ክልላዊ መንግስት ውስጥ ባከናወነው ሽብር። አዎ! የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ከዛሬ አንድ ዓመት ተኩል በፊት ገደማ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ከመካሄዱ ቀደም ብሎ በአፋር ክልል አርታሌ አካባቢ በተላላኪ አሸባሪዎቹ አማካኝነት የሀገራችንን ሉዓላዊ ግዛት

በመጣስ በሰላማዊ ቱሪስቶች ላይ ጥቃት ፈጽሟል፡፡ በዚህ እጅግ አረመኔያዊ ተግባሩም የአምስት ቱሪስቶችን ህይወት ቀጥፏል፤ ሌሎችም ታፍነው እንዲወሰዱ አድርጓል፡፡

የኤርትራ መንግስት ከአሸባሪነቱ አለመለወጡን የሚያሳይ ሌላ የቅርብ ጊዜ አብነትን ማንሳት እንችላለን። የአስመራ ጋዜጠኞች አቶ ኢሳያስን እንዲህ ሲሉ ይጠይቋቸዋል። …"በቅርቡ ስልጣን የያዙት የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ከኤርትራ መንግሰት ጋር ለመደራደር ዝግጁ ነን በማለት ላይ ይገኛሉ፤ ይህን እንዴት ይመለከቱታል?"…ታዲያላችሁ ሰውዬው ወትሮም ቢሆን ዓይናቸውን በጨው የታጠቡ በመሆናቸው፤ በትናንት አሮጌ እሳቤያቸው ውስጥ ሆነው እንዲህ ሲሉ የቅጥፈት መዓታቸውን ያዥጎደጉዱት ገቡ።…"የዚህ ጉዳይ መነሳት የህዝብን ትኩረት ከመሳብ የዘለለ ምንም አይነት ፋይዳ አይኖረውም" አሉ። አክለውም "የኤርትራ መንግስት በዚህ ድራማ ላይ ተሳታፊ መሆን አይሻም" በማለት ለሰላም የተዘረጉትን የኢትዮጵያን እጆች በእምቢተኝነት ባለመቀበል ዛሬም "ከፀረ-ሰላምነት የሚነጥለኝ ሞት ብቻ ነው" ብለው በአደባባይ እቅጩን ነግረውናል። ይህም የሻዕቢያ ሹማምንቶች እንኳንስ የባህሪ ለውጥ ሊያመጡ ቀርቶ ሽብርን እንደ ዕለት እንጀራቸው የያዙት መሆኑን የሚያመላክት ነው።

ሌላም ላክል። የአቶ ኢሳያስ መንግስት በአንድ ወቅት "ለመንገድ መስሪያ የሚሆን አሸዋ ለማምጣት ነው" በሚል ምክንያት የጂቡቲን ራስ ዱሜራ ኮረብታዎችን ወርሯል። ይህን ወራሪነቱን ግን ሊያምን አልቻለም–ዛሬም ድረስ ቢሆን። ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ግን ወራሪነቱን በማረጋገጥ ከጂቡቲ ሉዓላዊ ግዛት እንዲወጣ ለበርካታ ጊዜያት አስጠንቅቆታል፤ በወዳጅ በዘመድ አስመክሮታል፤ አስዘክሮታል። እርሱ ግን ምን ተዳው?...በሌሎች ሃብት ላይ ተንጠላጥሎ የማደግ ጥገኝነትን እንዲሁም ወታደራዊ ጀብደኝነትን ገና ካፈጣጠሩ ጀምሮ የተካናቸው ስለሆነ እነሆ እስካሁን ድረስ እንዳለ አለ። …እናም የሻዕቢያ ለውጥ ምን እንደሆነ የሚያውቀው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ብቻ እንጂ ማንም ሊሆን አይችልም።

የዚህን ፅሑፍ አቅራቢ እጅግ የሚያስገርመኝ ሌላኛው ጉዳይ፤ የአስመራው ቡድን ያለ አንዳች ባህሪያዊ ለውጥ 'የኢጋድ አባል ካልሆንኩ ሞቼ እገኛለሁ' ማለቱ ነው። መቼም አበው "አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው" የሚሉት ይሄኔ ሳይሆን አይቀርም። በመጀመሪያ ደረጃ ከኢጋድ ራሱን ያገለለው ሻዕቢያ ነው–የትብብር መድረክ የሆነውን ኢጋድ "መጠቃቀሚያ" ነው የሚል የዳቦ ስም በመስጠት።…ከዚያ በኋላም ቢሆን የኢጋድ

አባላት የኤርትራ መንግስት አባል መሆን እፈልጋለሁ ሲል በቅድሚያ እያከናወነ ካለው የሽብር ተግባር እንዲታቀብና ከአሸባሪዎች ጋር ያለውን ትስስር ማቆም እንዳለበት እንደነገረው ይታወሳል። ይሁንና አሁንም ሻዕቢያ ምንም ዓይነት ባህሪያዊ ለውጥ ሳደርግ በአሁኑ ወቅት የአባል ልሁን ጥያቄ ማንሳቱ ቅቡል አይደለም።

እርግጥ የአስመራውን ቡድን የአባል ልሁን ጥያቄን በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል–ካጋጠመው አጠቃላይ ለውጥና የኢጋድ አባል ሀገራትን ለማዳከም የዘየደው መላ መሆኑን። ነገሩም እንዲህ ነው።...ራሱን ቀስ በቀስ ከወራሪነት ወደ አሸባሪነት የቀየረውና እንደ መንደር ጎረምሳ የኢጋድን ቀጣና ሲበጠብጥ የነበረውና እየበጠበጠ ያለው ሻዕቢያ፤ ለቀጣናው ሀገራት ያበረከተው አንዳችም አዎንታዊ ነገር የለም፡፡ እዚህ ላይ 'ታዲያ አዲሱ አባል ካልሆንኩ ባህሪው ከየት የመጣ ነው?' ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ግና ለመልሱ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም– ሻዕቢያ "ሲሞቅ በማንኪያ፤ ሲቀዘቅዝ በእጅ" ዓይነት የሞኝ ዲፕሎማሲ የሚከተል ነውና፡፡ የአቶ ኢሳያስ አስተዳር ዛሬ በሁሉም መስኮች አጣብቂኝ ውስጥ ነው፤ ናላውም ዞሯል፡፡ በእነ ሙባረክና ጋዳፊ አማካኝነት ይገኝ የነበረው ጥቅማ ጥቅምና ድጎማ "ተረት" ሆኗል፡፡ እንኳንስ "ወዲ አፎምን" አይዞህ ሊሉ ቀርቶ፤ ለራሳቸውም አይዞህ ባይ አጥተው ዓለም ተደበላልቆባቸዋል– አንደኛው በቃሬዛ ፍርድ ቤት እየቀረቡ፤ ሌላኛው ደግሞ አብዮት በልቷቸዋልና። ከዜጎቹ በግዳጅ ይሰበስብ የነበረው የሁለት በመቶ የገቢ ታክስም በአንዳንድ መንግስታት አማካኝነት እየከሰመ ነው።

በዚህ ምክንያትም ሻዕቢያ መሳሪያ እየተቀበለና እያቀበለ የሚያፈነዳበት አቅሙ እየሟሸሸ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም፤ አል - ሸባብ የተባለው የሶማሊያ አሸባሪ ቡድን በሀገሪቱ የሽግግር መንግስትና የፀጥታ ኃይሎች አማካኝነት ከሞቃዲሾ 'ማቄን ጨርቄን' ሳይል እግሬ አውጪኝ ብሎ መፈርጠጡ የአስመራውን መንግስት "የሁከት ህልም" አምክኖታል፡፡ …ታዲያ ሻዕቢያ ምን ቀረው?– አዎ! የሽብር ስራው ሲቀዘቅዝ፤ የትናንት ኢጋድን ሲያወግዘውና ሲሳለቅበት እንዳልነበረ ሁሉ "የቀበሮ ባህታዊ" በመሆን 'አባል ካልሆንኩ' ማለት ብቻ ነው–የቀረው አማራጭ፡፡ ግና እንዲህ ዓይነቱ 'ሲመችኝ አፈነዳለሁ፣ ካልተመቸኝ ደግሞ አባል ሆኜ የኢጋድ አባላትን በመነጣጠል አዳክማለሁ' የሚል "ሲሞቅ በማንኪያ፣ ሲቀዘቅዝ በእጅ" ዓይነት የዕብዶች ዲፕሎማሲ በምንም ዓይነት መንገድ ተቀባይነት የለውም– ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ፣ አፍሪካ ህብረትም ይሁን ኢጋድ ለአሸባሪዎች ምንጊዜም ቢሆን በራቸው ዝግ ነውና፡፡

እርግጥ የኤርትራ መንግስት የኢጋድ አባል ልሁን የማለቱ ድብቅ አጀንዳ ከማንም የሚሰወር አይመስለኝም። ዋና ዓላማው ባህሪያዊ ማንነቱን ሳይተው አባል በመሆን ሀገራቱን ከፋፍሎ ማዳከም ነው። ግና ይህ ሌሎች ሀገራትን አሳንሶ የመመልከትና ራስን ከሳህል ተራራዎች በላይ አግዝፎ የማየት ሻዕቢያዊ በሽታ ከነባራዊው ሃቅ ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም። የአስመራውን አስተዳደር መቼም ቢሆን የማይቀየር ማንነትን የሚያውቁት የኢጋድ አባል ሀገራት ይህን ዓይነቱን የሞኝ ስሌት ጠንቅቀው ያውቁታል። አናም ፀብን እንጂ ትብብርን፣ ሁከትን እንጂ ሰላምን ለማይሻው የአቶ ኢሳያስ መንግስት የቀበሮ ባህታዊነት ሽርጉድን ከመጤፍ የሚቆጥሩት አይመስለኝም።

እዚህ ላይ ከአቶ ኢሳያስ የሽብር አጋፋሪነት አንፃር ሁለት አማራጮችን ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛው ሻዕቢያ የሽብርና የትርምስ ስትራቴጂውን ሙሉ ለሙሉ እርግፍ አድርጐ በመተው ከሰላም ወዳድ ኃይሎች ጋር መሰለፍ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በያዘው የግብረ-ሽበራና የብተና ስትራቴጂ መቀጠል ነው፡፡ ምንም እንኳን ምርጫው የሻዕቢያ ቢሆንም፤ በእኔ እምነት ግን ሻዕቢያ ሁለተኛውን አማራጭ ይገፋበታል ባይ ነኝ። ለዚህ ደግሞ በግልፅ የሚታወቅ ባህሪያዊ ዕውነታን ማንሳት ይቻላል። ይኸውም አቶ ኢሳያስ “የዕለት እንጀራቸው” የሆነውን ሽብርንና ትርምስን እርግፍ አድርገው በመጣል ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ልባቸው የማይቆርጥ ነው፡፡ እርግጥም 30 ዓመታት በበረሃ እንዲሁም 22 ዓመታት ደግሞ በመንግስትነት ቆይታቸው ያካበቱትን ይህን ተፈጥሮአዊ ማንነታቸውን አሽቀንጥረው ይጥላሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ አቶ ኢሳያስ ይህን ተግባር ይፈጽማሉ ብሎ ከማሰብ ይልቅ፤ “ወዳጃቸውና የነውጥ አጋራቸው የነበሩት ሆስኒ ሙባረክ ለሚቀጥሉት ዓመታት ግብፅን ይመራሉ” ብሎ መመኘት ቀላል ሳይሆን የሚቀር አይመስለኝም፡፡

በመሆኑም ማዕቀብን ለመከላከል ሲሉ የቀጣናውን ሀገራት አሸባሪዎችንና ፀረ-ሠላም ኃይሎችን ከአስመራ ማባረር አይችሉም፤ ድጋፍ ከመስጠትም አይቆጠቡም፡፡ እርሳቸው አሸባሪ ሆኖ ባለመስራት የሚያገኙትን የጥገኝነት ጥቅም ማጣት አይፈልጉም። እናም ነገሩ “ለወዲ አፎም” ከባድ ብቻ ሳይሆን፣ የህልውና ጉዳይ ጭምርም ነው ማለት ይቻላል፡፡ እናም በዚህ ሁኔታ ሽብርንና አሸባሪዎችን የሙጥኝ ብሎ የያዘ መንግስትን እንኳንስ

ማዕቀቡን ማንሳት ቀርቶ ሌላ ጠበቅ ያለ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባው በመንግስታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የሚገነዘበው ይመስለኛል–ራሱ ከመደበው አጣሪ ቡድን ውጪ ሌላ አሳማኝ እማኝ ሊያገኝ አይችልምና። ያም ሆነ ይህ ግን ሻዕቢያ አኳያ ሰሞነኛው ሪፖርት የሚታስተላልፈው አብይ ጉዳይ አለ። እርሱም ነፍሳቸውን ይማረውና “ከተያዝክ በኋላ የጥይት አረር ከመጠጣት ውጪ ምን ታደርጋለህ?” አሉ እንደተባሉት ጋዳፊ፤ አቶ ኢሳያስም አስቀድመው ከሽብር ተግባራቸው መቆጠብ እንጂ፣ እጅ ከፍንጅ ከተያዙ በኋላ ያለ አንዳች ተጨባጭ ባህሪያዊ ለውጥ ቢንፈራገጡ ድርጊታቸው ዋጋ ቢስ መሆኑን መገንዘብ ያለባቸው መሆኑ ነው።

በጥቅሉ የአስመራው ቡድን በእስከ ዛሬ ተግባሩ በለበጣ “የሶማሊያን የሽግግር መንግስት እንደግፋለን” እያለ ዓለም አቀፉን ማህበረሰብንም ይሁን ቀጣናዊ ትብብሩ ላይ ለማሾፍ ቢሞክርም፤ ምንም ዓይነት ለውጥ አላሳየም። እንዲያውም ቀደም ሲል የጠቀስኩት የተመድ አጣሪ ቡድን ሪፖርት የግብረ-ሽበራ ተግባሩን አለመተውን ነው ያረጋገጠው። ለነገሩ ሀገር መምራት በጀመረ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወራሪ፣ ኋላ ላይም አሸባሪ የሆነው የአቶ ኢሳያስ ቡድን፤ ቀጥተኛ ወረራ እንደማያዋጣው አውቆ የግብረ- ሽበራ ስትራቴጂን ቋሚ መተዳደሪያው ያደረገ ነውጠኛ ኃይል በመሆኑ ከዚህ ተግባሩ ሊቆጠብ አይችልም፡፡ ይህን ደግሞ እንኳንስ ትላልቆቹ ዓለም ዓቀፋዊና ቀጣናዊ ተቋማት ቀርተው የእኔ ዓይነቱ ተራ ዜጋም የሚያውቀው ነው።

እናስ አቶ ኢሳያስ በየጎራው እየዞሩና በቀጣፊነት የተካኑትን ዲፕሎማቶቻቸውን እያሯሯጡ “ማዕቀቡ ይነሳልኝ” ማለታቸው ከቶ ምን ይሉት ዲፕሎማሲ ይሆን?...የተለመደው “ዓይኔን ግንባር ያድርገው” ወይስ “ዓይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ” የሚል አጉል ብልጣ ብልጥነት?...መቼም ‘አጃኢብ’ እንጂ ሌላ ምን ይባላል?!...ያም ሆነ ይህ ግን ሻዕቢያ የውሸት አቆፋዳን ይዞ ሲሮጥ ተደናቅፎ ሊወድቅ እንደሚችልም ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት ያለበት አይመስለኝም–“ሲሮጡ የታጠቁት የውሸት ቋጠሮ ሲሮጡ መፈታቱ አይቀሬ ነውና።

–